የ2016 የበጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ ወቅታዊ መረጃ

# በት/ቤቶቻችን ሙአለንዋይ ፈሰስ ማድረግ፤ የውደፊታችንን ማረጋገጥ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ፌብሩወሪ 2015

ውድ ጓደኞች፣

የካዊንታችን ወደፊት በት/ቤቶቻችን የተመረኮዘ ነው—ት/ቤቶቻችንም በናንተ ይመረኮዛሉ።

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ የ2016 በጀት አመት የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ ለካውንቲው ስራ አስፈፃሚ አይዛያህ ለጌት (Isiah Leggett ) እና ለካውንቲው ምክር ቤት ለግንዝቤአቸው እያስገባ ነው። መጠነኛ የሆነ የ4% አካባቢ ጭማሪ ይዟል። የካውንቲ መሪዎቻችን በበጀታችን መወያየት በሚጀምሩበት ወቅት፣ ድምፅዎን ማሰማትና በትምህርታችን ፈሰስ ማድረግ በልጆቻችን እና በካውንቲያችን የወደፊት ፈሰስ ማድረግ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።

ከታወቀው ኤኮኖሚስት ከዶ/ር ስቴፈን ፉለር የቀረበ አዲስ ዘገባ ለ2016 በጀት አመት ለMCPS ሙአለንዋይ ፈሰስ የተጠየቀው ለMontgomery County ኤኮኖሚ ከ$3.26 ቢልዮን በላይ አስተዋፅኦ እንድሚያደርግና የስራዎችን ብዛት በአካባቢና በስቴቱ በሞላ ከፍ እንደሚያደርገው ያሳያል። (ስለ ዶ/ር ፉለር ዘገባ በዚህ ሰነድ ውስጥ በሌላ ቦታ ይበልጥ መማር ይችላሉ።)

የቦርዱ የ2016 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ በመሰረቱ ተመሳሳይ አገልግሎቶች በማደግ ላይ ለሚገኘው የተማሪዎች ቁጥር እንድናቀርብ ያስችለናል። በስቴቱ የትምህርት እርዳታ የ$10 ሚልዮን ቅናሽ መደረጉ አዲሶቹን ሙአለንዋዮች በሚያሳስብ ሁኔታ እንድንቆርጥ አስገድዶናል፣ በመንስራራት ላይ የሚታየውም የካውንቲ በጀት መጓደል በመምርያ ክፍል እንደገና ተጨማሪ ጉዳት ያስከትላል። ገንዘብ ለመቆጠብና የሚመጣውን አመት በጀት የገንዘብ መሚላት ለመደገፍ፣ በኖቬምበር ውስጥ በጀቱ እንዳይንቀሳቀስ አድርገናል። ይህ እርምጃ የበጀት ቁጠባችንን ወደ $33 ሚልዮን ከፍ አድርጎታል፣ ይህም የ2016 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀታችንን በገንዘብ ለማገዝ ይውላል።

ከ2009 ታላቁ የኤኮኖሚ ውድቀት ጀምሮ በእያንዳንዱ አመት፣ በጀታችንን ለቁጠባ እየዳሰስን፣ ቀበቶአችንን እያጠበቅን፣ እናም ከካውንቲያችን ያገኘነው በህግ አተፈቀደልንን አነስተኛ ጭማሪ ብቻ ነው። እነዚህን አስፈላጊ እውነታዎች አገናዝቡ፡-

- ከ2009 ጀምረን፣ ከ1,400 በላይ የስራ ቦታዎች ሰርዘናል፣ ከ$175 ሚልዮን በላይ እየቆጠብን። በዚያኑ ወቅት $140 ሚልዮን የደሞዝ ጭማሪዎች ለሌላ ጊዜ ተሸጋግረዋል።
- በዚያኑ ጊዜ፣ ከ17,000 በላይ በሚሆኑ ተማሪዎች አድገናል፣ አብዝኛዎቻቸው ተጨማሪ አገልግሎቶችና ድጋፍ ፈላጊዎች የሆኑ።

የ2016 በጀት አመት በጀታችን ፈጣን ማጠቃለያ የተማሪ ግኝት ለማሻሻልና ክፍተት ለመዝጋት እንዴት የሙአለንዋይ ፈሰስ እንዳደረግን ከተወሰን መረጃ ጋር ለርስዎ መጣቀሻ እዚህ አካትተናል።

ቦርዱ ት/ቤቶቻችን ከሁሉም በላይ የላቀውን ትምህርት እንዲያቀርቡ አስፈላጊ መገልገያዎች እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ ግዴታ ገብቷል። ፖሊስ፣ የእሳት አደጋ፣ ቤተመፃህፍት እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን የመሳሰሉ ጎልተው የምታዩ በርካታ አገልግሎቶች ምክንያት Montgomery County ለመኖር ታላቅ ቦታ መሆኑን እናደንቃለን። ነገር ግን የኛ ወደፊት ልጆቻችን በወደፊታቸው ለመበልፀግ የሚያስፈልጋቸው ችሎታና ዝግጅት እንዲኖራቸው በማረጋገጥ ላይ እና የማህበረሰባችንን ጥንካሬ በመጠበቅ ላይ የተመረኮዘ ነው። እባክዎ ይህን መረጃ ድህረ እይታ ያድርጉበትና የካውንቲ መሪዎቻችን በልጆቻችን ሙአለንዋይ ፈሰስ በማድረግ መቀጠል አስፈላጊ መሆኑን እንዲያውቁ በማድረግ ያግዙን።

ከአክብሮት ጋር፣

Patricia B O'Neill

Patricia B. O'Neill (ፓትሪሽያ ኦ'ኔይል)ፕሬዚደንት
የMontgomery ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

# ፈጣን እውነታዎች ስለ የቦርድ የ2016በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ

**የMONTGOMERY COUNTY የትምህርት ቦርድ** ለ2016 በጀት ዘመን (የ2015-16 የትምህርት አመት) የ$2.39 ቢልዮን የስራ ማስኬጃ በጀት እየጠየቀ ነው። ይህ ከውቅቱ በጀት የ4.1 በመቶ የወጪ ጭማሪ ($93.4 ሚልዮን) ነው፣ ከበጀቱ 99 በመቶው ለከፍተኛ የተማሪዎች ቁጥር ተመሳሳይ አገልግሎት ለመስጠት እየዋለ። የካውንቲው ምክር ቤት፣ የጡረተኞች የጤና ጥቅሞች የሚደጉመውን አካውንት ጨምሮ፣ ለ2015 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ተጠቅሞ የነበረውን ያንድ ጊዜ ምንጮች ለመተካት $23.3 ሚልዮን በተጨማሪ ያስፈልጋል።

በካውንቲና በስቴት ደረጃዎች ከተገመተው የገንዘብ እጥረት ጋር፣ ይህ መጠነኛ የወጪ ጭማሪም አጠራጣሪ ሆኖ ይገኛል።

የ2016 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ የሶስተኛ አመት ባለ-በርካታ-አመት የበጀት ስልት ለሚከተሉት የተተለመ ነው—

- ቀጣይ እድገትን ማስተዳደር፣
- የግኝት ክፍተቶችን፣ ማጥበብ፣ በመጨረሻም መዝጋት፣ እና
- ተማሪዎችን ለወደፊት ለማዘጋጀት ፈጠራን/ግኝትን መንከባከብ።

## የ16 በጀት ዘመን የስራ ማስከጃ በጀት የገቢ ምንጮች

**(በሚልዮኖች)**




## እድገትን እና ተጨማሪ ዋጋዎችን ማስተዳደር

**MCPS** በየአመቱ ከ2,000 በላይ በሚሆኑ ተማሪዎች እያደገ ነው። የቦርዱ በጀት ባጭሩ አብዛኛው MCPSን ለተጨማሪ ተማሪዎች ተመሳሳይ ደረጃ አገልግሎቶች እንዲያቀርብ ያስችለዋል። በዚህ አመት፣ ይህን የምዝገባ እድገት ለመቋቋም ብቻ MCPS 270 የስራ ቦታዎች መጨመር ያስፈልገዋል።

- 111 የኤሌሜንታሪና የሁለተኛ ደረጃ የስራ ቦታዎች
- 96 የልዩ ትምህርት የስራ ቦታዎች
- 41.5 የስራ ቦታዎች የEnglish for Speakers of Other Languages (እንግሊዘኛ ለሌሎች ቋንቋ ዎች ተናጋሪዎች) (ESOL) አገልግሎቶች የሚቀበሉ ተማሪዎችን ለማገልገል፣ እና
- 25 የስራ ቦታዎች ለትራንስፖርት።

ከጭማሪው የተቀረው፣ ለMCPS ሰራተኞች የማካካሻ ጭማሪዎች፣ ለወቅቱ ሰራተኞችና ጡረተኞች ጥቅማጥቅሞች፣ ትራንስፖርትና ለስራ ወጭዎች፣ አቅርቦቶች፣ ቁሳቁሶች፣ እና ቴክኖሎጂን ጨምሮ ቀጣይ ወጭዎችን በተጨማሪ ይሸፍናል። ከወጪ ማቆም፣ የበጀት መቆረጦች፣ እና ለጤናቸው ጥቅሞች ወጪ ከሰራተኞች የሚደረጉ ተጨማሪ አስተዋፅኦዎች የተገኙ ቁጠባዎች በጀቱን ለማሟላት ያግዛሉ።

## ፍይናንሳዊ ፈታኞች/ተግዳሮቶች

**MCPS ፕላን ያደረገው** ከስቴት ለትምህርት እርዳታ የ$15.8 ሚልዮን ነበር፣ ነገር ግን ከመንግስት የተቀበለው የ$10.3 ሚልዮን መቆረጥ ነው። በLawrence J. Hogan, Jr (ሎውረንስ ጄይ. ሆጋን፣ ጁ/ር) የቀረበ የስቴት በጀት። በዚያኑ ወቅት፣ Montgomery County ባለስልጣኖች ካውንቲው የ$200 ሚልዮን እጥረት በመግጠም ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ካውንቲው ቢያንስ ቢያንስ $30.8 ሚልዮን ጭማሪ ገንዘብ በምዝገባ እድገትና በጡረታ ግዴታዎች ሂሳብ ለMCPS እንዲሰጥ የስቴት ህግ ይደነግጋል። ነገር ግን ፍላጎቱ እጅጉን ብዙ ነው፣ የቦርዱ በጀትም $84.7 ሚልዮን የስቴት ህግ ከሚጠይቀው ከዝቅተኛ ደረጃ የበጀት ምደባ በላይ ይፈልጋል። ካውንቲው በዚህ ደረጃ ካላቀረበ፣ MCPS ለት/ቤቶችና ከፅ/ቤቶች ይበልጥ ተሰሚነት ያላቸው ቅናሾች እንዲያደርግ ይገደዳል።

## ከት/ቤቶች ሊኖሩ የሚችሉ ቅናሾች

**MCPS የሚመድበው** ከሚመጣው አመት የ350 የስራ ቦታዎች ከት/ቤቶች መቆረጥ—በዚህም የበጀት እጥረቱን ምላሽ ለመስጠት የ25 ሚልዮን ቁጠባ። የቦርዱ በጀት የበላይ ተቆጣጣሪው ለስልታዊ ማሻሻያ አቅርቦት የነበረውን ትርጉም ባዘለ ሁኔታ በተጨማሪ ቀንሶታል፡-

- የበላይ ተቆጣጣሪው አቅርቦት የነበረው ለ78 የስራ ቦታዎች የ$8.2 ሚልዮን ለስልታዊ መሻሻል ሲሆን የቦርዱ በጀት ጥያቄ ግን ለ20 የስራ ቦታዎች የ$2.5 ሚልዮንን ያካተተ ነው።

# የግኝትን ክፍተት ለመዝጋት ሁሉአቀፍ ፈሰስ ማድረግ

**እያንዳንዱ ዶላር** በMCPS የስራ ማስኬጃ በጀት ውስጥ የተተለመው ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት ነው/። ቢሆንም፣ MCPS ገንዘብን በልዩ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች፣ እና የግኝትን ክፍተት ለማጥበብ—በመጨረሻም ለመዝጋት—ባተኮሩ አነሳሽነቶች ላይ ያውለዋል።

የቦርዱ የ$2.39 ቢልዮን የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ ትልቅ ክፍል የግኝትን ክፍተት ለመዝጋት የዲስትሪክቱን ጥረት በቀጥታ የሚደግፉ ገንዘቦችን ያካትታል። ለምሳሌ፣ MCPS በድህነት ይበልጥ በተጠቁት 69 የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ተጨማሪ ገንዘብ ለማቅረብ በመቀጠል ላይ ይገኛል። እነዚህ ት/ቤቶች፣ ከሌሎች ት/ቤቶች በአማካይ ከ$2 ሚልዮን በላይ ይቀበላሉ፣ ይም ቅድመሙአለህፃናት ፕሮግራሞች ለማቅረብ፣ በዝቅተኛ ክፍሎች አነስተኛ የተማሪ ብዛት፣ በስነፅሁፍ ክሂሎቶች ያተኮሩ ተጨማሪ ሰራተኞች ማቅረብ፣ እና የተማርዎችንና የቤተሰቦቻቸውን ራፐአራውንድ ፍላጎቶች ለማሟላት አገልግሎት ላይ ይውላል። በ2016 በጀት ዘመን የበጀት ፕሮግራም እንደተዘገበው፣ የቦርዱ የበጀት ጥያቄ ሲሶ አካባቢ ($787.6 ሚልዮን) የግኝት ክፍተቱን ለመዝጋት ጥረቱን በተለይ በሚመለከቱ በሚከተሉት ሶስት መስኮች ላይ ነው፡-

## ተማሪዎችን ለመደገፍ ወጪ
(በሚልዮኖች)




## የተማሪን ግኝት ማሻሻል

- የተማሪን ግኝት ማሻሻል ተጨማሪ ድጋፍ የሚሰጡ ፕሮግራሞች (በ2016 በጀት ዘመን $637.4 ሚልዮን)፡- እነዚህ ለተማሪዎች ከዋነኛ የትምህርት ፕሮግራም ባሻገር ቀጥተኛ አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ልዩ ትምህርት፣ የሰመር ትምህርት፣ የተማሪ አገልግሎቶች የመሳሰሉ ፕሮግራሞች እና በየክፍል ደረጃ የተማሪን ግኝት የሚያሻሽሉ ዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች ናቸው።

## ክፍተቱን ለመሸፈን የሁሉአቀፍ ፈሰስ
በ(ሚልዮኖች)




## የትብብሮሽ ሽርክናዎች

- የትብብሮሽ ሽርክናዎች ፕሮግራሞች የተማሪን ግኝት ለማሻሻል (በ2016 በጀት ዘመን $15.1 ሚልዮን)፡- እነዚህ ፕሮግራሞች የሚተዳደሩት እንደ ከትምህርት ሰአት በኋላ ፕሮግራሞች፣ የቋንቋ እርዳታ፣ ቤት ለሌላቸው ተማሪዎች እርዳታ፣ እና ለMCPS ቤተሰቦች የጤና እንክብካቤና ሌሎች አገልግሎቶች ለማቅረብ ሽርክናዎች የመሳሰሉ የልጆችን አካዴሚያዊና ማህበራዊ ስኬት የሚደግፉ ከሌሎች የመንግስት፣ የቢዝነስ፣ እና የማህበረሰብ ተቋሞች ጋር በመተባበር ነው።

## የት/ቤት መሻሻል መደገፍ

- የት/ቤት መሻሻልን እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የሚደግፉ ፕሮግራሞች ($135.1 ሚልዮን)፡- እነዚህ ፕሮግራሞች የት/ቤት መሻሻል፣ የባለሙያ ትምህርት፣ የአመራር ብልፅግና፣ ቅጥርና ምስክር ወረቀት መስጠት፣ እና ግምገማና ምርምር ያካተተ በከፍተኛ ደረጃ በባህል የበለፀገ ትምህርት ለመስጠት የት/ቤቶች ችሎታና ሰራተኞች ለመገንባት የተተለሙ ናቸው።

# ለ2016 የበጀት ዘመን ስልታዊ መሻሻሎች

**ባለፉት ሁለት አመቶች** (2014 እና 2015 የበጀት ዘመኖች)፣ MCPS የግኝት ክፍተት ፀንቶ ያዘወተረባቸውን መስኮች ለመጋፈጥ ባተኮሩ ስልታዊ መሻሻሎች ላይ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች ሙአለንዋይ አፍስሷል። ከነዚህ ሙአለንዋዮች መካከል የተማሪዎችን እንግሊዘኛና ሂሳብ አፈፃጸም ለማሻሻል ከ50 በላይ የሆኑ የሁለተኛ ደአጃ ት/ቤት "ትኩረት" መምህራን፤ 10.5 የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብልፅግና መምህራን ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፤ 17 የኤሌሜንታሪ መምህራን የሂሳብ ትምህርት ለማሻሻል፤ 23.5 አማካሪዎች፣ የት/ቤት ሳይኮለጂስቶች፣ እና ፒዮፐል ፔርሶኔል ሰራተኞች፣ እና ግምት የሚሰጣቸው ሙአለንዋዮች በመምህር አመራር እና በት/ቤት-በተመሰረተ የባለሙያ ትምህርት። የሚከተሉት በቦርዱ የ2016 የበጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ ከተካተቱት ስልታዊ መሻሻያዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡-

- 6.5 የኤሌሜንታሪ ት/ቤት አማካሪዎች፣ የት/ቤት ሳይኮለጂስቶች፣ እና ፒፐል ፐርሶኔል ሰራተኖች፤
- 5.0 የሂሳብ ይዘት አሰልጣኞች የኤሌሜንታሪ ት/ቤት ሂሳብ አፈፃፀም ለማሻሻል፤
- የካውንቲና የማህበረሰብ ሽርክናዎች ለማዳበር ገንዘቦች፤
- ርትአዊ ስልጠና እና የመምህራን የስራ ሀይልን ለመደገፍና በአይነት ለማባዛት ለማገዝ ገንዘቦች፤
- 6.0 የስራ ቦታዎች ከት/ቤት ውጭ Interim Instructional Services (መሸጋገርያ የትምህርት አገልግሎቶች) ለሚቀበሉ ተማሪዎች አገልግሎት ለመጨመር፤ እና
- የESOL አገልግሎቶች ለሚቀበሉ ተማሪዎች በተሻለ ለማገልገል ለሰራተኞች የበለፀገ/የተሻለ ስልጠና።

**ስለ የMCPS የስራ ማስኬጃ በጀት ተጨማሪ መረጃ፣**
www.montgomeryschoolsmd.org ይጎብኙ፣ "budget"ን ይፈልጉ።

አዲስ ዘገባ፡-

## MCPS ለካውንቲውና ለስቴቱ የኤኮኖሚ ሞተር ነው።

**አንድ ዘገባ** በታወቀው የኤኮኖሚ ሊቅ ዶ/ር ስቴፈን ፉለር MCPS ለሞንጎመሪ ካውንቲና ለሜሪላንድ ስቴት የስራና የገቢ አይነተኛ ምንጭ ነው ብሎ ያጠቃልላል። በጆርጅ ሜሶን ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ትንተና ማእከል ዳይረክተር የሆነው ዶ/ር ፉለር፣ የ2016 በጀት አመት የMCPSን የስራ ማስኬጃና የት/ቤት ህንፃ ስራ በጀቶችን የኤኮኖሚ ተፅእኖ አጥንቶ የቀረቡት ገንዘቦች—

- ለሞንጎመሪ ካውንቲ ኤኮኖሚ $3.26 ቢልዮን እና ለስቴት ኤኮኖሚ $4,1 ቢልዮን ያበረክታል፤
- በሞንጎመሪ ካውንቲ ለሚኖሩ ሰራተኞች (በበጀቱ ውስጥ ከተካተቱት የስራ ቦታዎች ባሻገር) $711 ሚልዮን አዲስ የግል ገቢ ይፈጥርላቸዋል፤
- በሞንጎመሪ ካውንቲ በድምሩ አመቱን በሞላ ለ17,388 ቋሚ ሰራዎች እና በሜሪላንድ ስቴት በሞላ ከ30,000 ስራዎች በላይ ይደግፋል፤ እና
- ማንም የግል ስራ ክፍል ቀጣሪ ከMCPS በላይ በሀገሪቱ ኤኮኖሚ የበለጠ ተፅእኖ ያለው አለመኖሩን ያመለክታል። በውነቱ፣ ከፌደራል መንግስትና ከካውንቲው አስተዳደር ባጠቃላይ ቀጥሎ MCPS ሶስተኛ እጅግ በጣም አስፈላጊ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው።

MCPS ከግብር ከፋዩ ሙአለንዋዮች ጠንካራ የትምህርት ተመላሽ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ስራዎች እንደሚፈጥር፣ ገቢ እንደሚያሳድግ፣ እና የካውንቲአችንና የስቴታችንን የወደፊት ስኬት እንደሚደግፍ ዘገባው ያሳያል።